# ምጽአት

By: cosmos-2000, June 2009

ካገሩ የወጣ አገሩ እስኪመለስ...መባሉን እያወቀች
ያልፍልኛል ብላ ሕፃን ልጇን አቅፋ ስደትን መረጠች::
መከራ በዝቶባት መምረጥ ተገደደች ካለመኖር መኖር
ከሰው ላይ ሰው ጭነው በታንኳ ታጭቃ ወደ ውጭ ስትበር
ሜዲትራንያን ግብር አስከፈለ ቀንቶ በቀይ ባሕር::
ወያኔን ቢጠሉ ሄዱ ወደ ስደት ውሃው ይብላን ብለው
ከሞት እየሸሹ ወደሞት ይጓዟል ይሏችኋል ይህ ነው::

ወጣት አበቦችም በጠራራው ፀሐይ ተሸጠው ሲሄዱ
እንደ ሰው ሰው መሆን አቃታቸውና ስንቶች ተዋረዱ::
ወተሸ እንዳትጠፊ አቤት እንዳትይም በሩን ቆልፎብሽ
ምግብ አዘጋጅተሸ ደክሚታል ሳትባይ ዕቃውን አጣጥበሽ
ወጥቶ ለመጫወት ከጓደኞችሽ ጋር እረፍት የት አግኝተሽ::
የባርነት ኑሮ እንድትኖሪ አውቃለሁ የቁም ስቃይ አይተሽ
ለማይቀረው ሞቱ መገላገል ፈለግሽ ሕይወትሽን አጥፍተሽ::

ተቆርቋሪ ቢያጡ በአራቱ ማዕዘናት ሄዱ ተሰወሩ
በየደረሱበት ምግባረ ብልሹ ተብለው ተጠሩ::
ለነፃነት ሞተው ተተኪውን ትውልድ እንዳላስከበሩ
ልጅማ አላወጡም ተወልዶም ይሆናል ይታያል ተግባሩ::
እንኳን ለራሳቸው ለአፍሪካ ነፃነት ለትግል ቀስቅሰው
ታሪካቸውማ በዓለም ተመዝግቧል አንድም ሰው አይክደው::
ለጥቁሮች ማኅሪያ ቅኝ ገዢዎቹ እስርቤት ሲሠሩ
ቅኝ ገዢው ሳይገባ ኢትዮጵያውያኑ እየገቡ ታኅሩ
እንዳርበኞች ቢሆን ይታያቸው ነበር ዱሩ ሸንተረሩ::

በርከት ያሉ ናቸው የነፃነት ትግልን በጧት የጀመሩ
ማቸነፍ ማለትን ሳያውቁ ተጉዞው በውር በድንብሩ
ሃቅን ስለያዝን ለማቸነፍ በቃን የሚሉት ዲስኩሩ
ጬኸትማ ሰማን የወያኔዎችን ሃሰት ሲናገሩ::
ሃቅማ ቢይዙ ፀሃይ እየወጣች ብርሃን እናይ ነበር
አንደበት ተዘግቶ ታስረን ተባረርን በራሳችን አገር
ዘረኛና አጃቢው ሲሆኑ አየናቸው ምሰሶና ማገር::

ላንድነት የሚቆም በመስዋዕትነቱ አቅርቦና ስቦ
መታመን በተግባር መታፈር በከንፈር ብሎ ተረባርቦ
በሃቅ እየዘገቡ ለጋራ ጥቅማችን ሥራውን መዝግቦ
ከወረደው ጥበብ “አንድ ሰው አስቦ አንድ በሬ ስቦ”
ልቦና ለሰጥው ፍንትው ይልለታል ከፊታቸው ቀርቦ::

ሹክ ብላቸውም መልስ አልሰጠኝ አሉ በዝቶ ውኾርንብሩ
በማኝ ፊት ብናገር ብናርፍ ይሻለናል ብለው ተሰወሩ
ፈርተን ነው ካላሉ እኛ የማይገባን ምንድን ነው ሚስጥሩ?
እናብር ስንለው እኔ ተቀብሬ መገኘቱን ይሻል ካዘኑ ከቀብሩ
ዝምታ ወርቅ ነው መባል ይቁም በቃ በርትቷል ችግሩ::

በሰከሩ ቁጥር ሚገድሉን ከሆነ እስቲ ምቱ መላ
ዓይናፋር ይመስል ዝምታን ስትመርጡ ሕዝቡ እየተቆላ
ሂዱ ተተፍተፉ እንዲወጣላችሁ የሰው ዓይነ ጥላ::
ስልቱ ገድሎ ማዳን ግንባር ቀደም ሆኖ ካሳየን አጉልቶ
አነጣጥረህ ምታ ደግ ነህ አልተባልክ አድሮና ሰንብቶ::
የሚጽፍም ይጻፍ ሸንጎ ፍጠሩና እስቲ ተማከሩ
አትሸፋፍኑት ይታወቅ ሰው-በላው ሰይጣናዊ ምክሩ::

ዝምታ ወርቅ ሚሆን:- ተስፋ ሲደርቅ ነው ወይስ ሲለመልም?
ተስፋማ ይለመልም ነጣጣይ ዘረኛ ካገር እንዲል እልም::
ተስፋንማ ሥሩ ጥቂት በጥቂቱ እኛም ደጀን ሆነን
ዕውን የሚሆነው ግፈኛ ተመቶ አገሩ አገር ሲሆን::

ምኞታችንን ገድሎ ስጋችን ጨረሰው እየዋለ እያደረ
አለመያዝ ደጉ አለመቀደም የተያዘው ሁሉ እንደወጣ ቀረ::
የጾሃፊን ብዕር በጉልበት አባሮ  ሃሳብ እየቀበረ
ጅሉም ስላልገባው ግፈኛውን አምኖ ሕይወቱን ገበረ::

ያውም በኛው አገር አሠሩን ገሰሱን እሥረኛ ይበላል
የሚቀምሰው አጥቶ ሕዝቡ በየተራ በረሃብ ክልትው ይላል
የሕዝባችንን ኑሮ ዓይናችን ዓይቶታል ልቦናችን ያውቃል
እንዲያው የለየለት ቁርጡ የታወቀው የእሥረኛው ይሻላል::
ትምህርት ቤት ገባሁ ገጠሩንም አየሁ ዙሬ ተዟዙሬ
አብሮ መኖር ተማርኩ ትዳርን መስርቼ ሥራም ተቀጥሬ
ውቅያኖስ አየሁኝ ባሕር አቋርጬ ውጭ አገርም ኖሬ
አገር በማጥፋቱ ወያኔን የሚያስንቅ አጣሁኝ መርምሬ::

ነግደው:- ለምነው:- በተገኘው ገንዘብ አጋዚን ተመቸው
በገደሉ ቁጥር ብሶባቸው መጡ ደም እየጠማቸው
የወገናችን ደም መጠጣት ሲበዛ ስካሩ አዞራቸው::
ለማምነው ሲያመጡ በገንዘቡ ብዛት ጎረቤት ወረሩ
አማራም አልቀረ ኦሮሞ ሶማሌ አኝዋክና አፋሩ
ሲዳማና ትግሬው የከታማው ነዋሪ እንዲሁም ገጠሩ
በእብሪት ተወጥረው ማን አለብኝ ብለው አገር መነጠሩ::

ከሃዲና ባንዳ አገር አከሰረ ባንኩንም ዘረፈ
ሚቆረቆር መስሎ የልቡን እየሠራ ፍትሕ አዛነፈ::
ታሪክን ሰርዞ ለሰንደቃላማው የግል ትርጉም ሰጥቶ
በመዝሙር ሲያጅቡ ጆሯችንን ደፈንን ጩኸቱ በርትቶ
ቢውለበለብ ቅሉ በልብ አናቅፈውም የኛን ትርጉም ትቶ::

እራሱ አጽድቆ እራሱ ከልክሎ መብትን አፈነና
አየር ደመናውን ሰማዩን ለማየት ቀና በሉ አለና
ካለእኔ በስተቀር ከአናታችሁ በላይ ከቶ ማን ቆመና
ዝናቡም የኔ ነው ውሃ የቋጠረን ማንሳፍፍ ደመና::
በነጎድጓድ ድምጼ ፍጡራንን ሁሉ ማኖር አሸብሬ
መብረቁን ሳባርቅ ስሃሊለነ ብለው ይስገዱ ወደ እግሬ
ከዋክብትን እዩ የዘራኋቸውን ወጥሬ ገትሬ

ጨረቃንም ሰጠሁ ማማረራችሁን ስለሰማሁ ወሬ::
የሁሉም ማዕከል ፀሓይማ እኔ ነኝ እምቦለሌ ማዞር
ምንም ሳላዛንፍ ጨለማና ብርሃን ወቅቱን ማቀያይር
ሙቀት እየሰጠሁ እፅዋት ለምልመው ሚበላ የምቸር::

ይህን ሁሉ አድርጌ ሊፈትነኝ መጣ ጉልበቴ ተንቆ
አቅሜን ላስመሰክር  ከአፋር በሚነሳው የሽምጥ ሸለቆ
አለቱን ብረቱን አንድ ላይ አቅልጨ ገድል ልሥራ ብዬ
እንደ ማንዳ ሃራሮ እሳተ ገመራ ወደላይ ገንፍዬ
እንደ ዳላፊላ የእሳት አለሎውን አውጥቼ አንቀልቅዬ
ምድርን ያለምሰሶ ሰማይን ያለ ባላ ቀጥ አርጌ አቁሜ
ጉልበቴን ፈርታችሁ እንድትሰግዱልኝ ነው ይህ ሁሉ ድካሜ::

ልባችሁ ሸፍቶ ጌታ ሆይ ብላችሁ መች እኔን ጠራችሁ?
ከእኔ በላይ ላሳር ክብሬን አትጋፉ አሁንስ ገባችሁ?
ቁጣዬ በርትቶ ደጋግሜ ሞከርኩ ክንዴን ላሳያችሁ::
ለምድራዊ ስልጣን ቀናዒ መሆኔን ያዳም ዘር እንዲያውቅ
ዕድሜዬ ሚረዝመው በእኔ ሥር ሲውል ነው ያገሪቱ ወርቅ::
ሁለቱን እሴቶች ከመዳፌ አውጥቶ የሚወስድ ከመጣ
የጦር ሠራዊቴ እርምጃ ይወስዳል የለብኝም ጣጣ::

ቢረገም ነው እንጂ ሰይጣን መልአክ ነበር ብለው ያስተማሩኝ
ዕውነት እንደሆነ በሕይወት እያለሁ ይኸው ተረዳሁኝ::
አላቂነታቸው አልታይ ብሏቸው በትዕቢት ቀጠሉ ግፉን ሰቆቃውን
እንዴት ቢንቁን ነው?....እየጠሉ ገዙን ደንቆሮ አድርገውን::
ፈጣሪን በማመን በደም ባጥንታቸው ወያኔን ሊያባሩ
ያልሰማህ ከሆነ ከተነሱ ባጁ ሃሞተ ኮስታሮች የማይበገሩ::
ጥቂቶች ቢሆኑም ሕዝባቸውን አምነው ፈተናውን አልፈው
ሳይንበረከኩ ጥርት ባለ ራዕይ ባላማ ታጅበው
ከፈጣሪ ታዟል የነፃነት ቀንዲል ሊያበሩ ከፍ አርገው::

እንደ እግዚአብሔርም ሕያው ነኝ ሁሉን አደርጋለሁ
ሕዝብ እንዲገዛልኝ የፈጣሪ ጥበብ ይኸው ይዣታለሁ
እያለ ቀባጥሮ እምብዛም አይቆይም እንደ ጉም ይበናል
በእርሱ መቃብዕር ላይ ጥበብም ጉልበትም የሕዝቡ ይሆናል::
መኖር መደምሰስም በእኔ ፈቃድ ነው ሲል
መነሻውን ሳያውቅ የፈጣሪን ጥበብ የያዛት ሲመስል
ምንድነው ዝምታው ከሕዝብ ጋር ሆነን ዘግ ማድረግ ስንችል
ጤና የሚገኘው መዝምዘን ሰርስረን ገርስሰን ስንጥል::